# *በሰሜን ኣሜሪካ ዉስጥ በቦስተን፣ በሜይንና ከነቲኬት ከምንኖር* *ኢትዮጵያዊያን የተሰጠ የሐዘን መግለጫ*

*ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ከወጣትነት ዕድሜያቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ ህልፈታቸው ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት፣ ለእምነት ነፃነት፣ ለዲሞክራሲያዊና ፌደራላዊ ሥርዓት መገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ታላቅና አርቆ አሳቢ መሪ ነበሩ። የኒህንም ታላቅ መሪያችን ድንገተኛ ዕረፍት ከሰማንበት ጊዜ አንስቶ በቦስተን፣ ሜይንነ ከነቲኬት የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ጥልቅና መራር ሐዘን ተሰምቶናል።*

*ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ብሎም በዓለም ዙሪያ ትልቅ ራዕይ አንግበው የተንቀሳቀሱ፣ አንቱ ከተባሉ በዓለም ከታወቁ መሪዎች ጎን በመሰለፍ እናት ሀገራችን ኢትዮጵያን በዓለም የነበራትን ገፅታ ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር፣ በትምህርት፣ በጤና በማኅበራዊ ጉዳይ በተለይም የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ከኋላ ቀርነት በማላቀቅ፣ ፈጣን ዕድገት በማምጣት ላይ ካሉ ጥቂት አገሮች አንዱዋ እንድትሆን ያስቻሉ ብልህ፥ አስተዋይና ታላቅ መሪ መሆናቸውን እናውቃለን።*

*ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ለሰላም ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለያዩ የአፍሪካ ኣህጉራት የእርስ በርስ እልቂት እንዲገታ፡ የኢትዮጵያን ሠራዊት በአፍሪካ ኅብረትና በተባበሩት መንግሥታት የሰላም ተለዕኮ በብቃት የሚወጣ ኃይል ያሰለፉ መሪ ናቸው።*

*ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ በተለይ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በሀገራችን ጉዳይ ንቁ ተሳትፎ እንድናደርግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የዲያስፖራ ጉዳይ ጽህፍት ቤት በማቋቋም ብዙ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው ኢንቬስትመንት በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲሳተፉ አድርገዋል።*

*እኛ በቦስተንና አካባቢዋ እንዲሁም በሜይንና ከነቲኬት የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ታላቁ መሪያችን በአካል ቢለዩንም አቅደውትና ወጥነውት የሄዱትን ብሩህ ራዕያቸው ከእኛ ጋር እንዲኖርና ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላችንን ድርሻ እንደምንወጣ ቃል እየገባን ለመላው ቤተሰባቸው ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ብርታቱንና መፅናናቱን እንዲሰጣቸው እንመኛለን።*

**August 26, 2012,** *U.S.A, ከቦስተን ከተማ*